# ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ መረጃ እና የመውጫ-ምርጫ ቅጽ

*ታተመው፥ ኦገስት. 27፣ 2021*

ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ስምምነት ቅጽ። የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ትምህርት ቤቶች የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ኬዞችን በፍጥነት እንዲለዩ እና የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ስርጭትን በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲቀንሱ ይረዳል። **ለ 2021-22 ትምህርት ዓመት፣ የተማሪዎ ትምህርት ቤት ለዲሲ የህዝብ እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የቀረበውን የከተማ-ደረጃ ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ውስጥ እየተሳተፈ ነው።**

ይህ ፕሮግራም ሳላይቫ-ላይ የተመሰረተ PCR ምርመራን ይጠቀማል፣ እዚህ የበለጠ መማር የሚችሉትን፥ www.shieldt3.com/k12/። የምርመራ ውጤቶች ለተማሪ ወላጅ/ሞግዚት(ወይም በቀጥታ ለአዋቂ ተማሪ)፣ ተገቢ የትምህርት ቤት ባለስልጣን(ኖች)፣ እና DC Health (ዲሲ ሄልዝ) ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ይጋራል።

የከተማ ደረጃ ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ የዲሲ የሕዝብ እና የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችስለ ምርመራ ፕሮግራሙ መረጃን ከእርስዎ እና ከተማሪዎ ጋር ለማጋራት እና ደታን ለተዛማጅ ባለስልጣናት ለማጋራት ይህን ቅጽ እየተጠቀሙ ነው። **ሁሉም ምርመራ በነጻ ነው።**

ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የምርመራ ፕሮግራም ሁለቱም ምልክት-ያለው እና ምልክት-አልባ ምርመራን ያቀርባል። ምልክት-አልባ ምርመራ ተማሪ የ COVID-19 ምልክቶች ባይኖረው/ራት እንኳ የ COVID-19 ምርመራ ማድረግ ነው፣ መደበኛ የ "ማጣሪያ" ምርመራን ጨምሮ። ለ 2021-22 ትምህርት ዓመት መጀመር፣ በዘፈቀደ የተማሪዎች ናሙና ለምርመራ በየሳምንቱ ይመረጣሉ። እንዲሁም የምልክት-አልባ ምርመራ የ COVID-19 ፖዘቲቭ ኬዝ የቅርብ ግንኙነቶችን ይጨምራል። እርሱም የበሽታው ስርጭትን ለማሳየት ውጤታማ ስልት ነው እና ሊከሰቱ የምችሉ ወረርሽኞችን አስቀድሞ ለመለየት ሊደግፍ ይችላል። ይህ ለተማሪው/ዋ በፍጥነት ለ COVID-19; ተመርምሮ/ራ ፖዘቲቭ ከሆነ/ች እንክብካቤ ለመስጠት ያግዛል፤ ተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ እና ማህበረሰቡን ይጠቅማል፤ እና በ-አካል ትምህርት ውስጥ ድጋፍ ይቀጥላል። ምልክት-ያለው ምርመራ ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት እያለ/ች የ COVID-19 ምልክቶችን ካሳየ/ች የሚደረግ ምርመራ ነው።

**ምርመራው ምንድን ነው?** ምርመራ አካልን-የማይወጋ የPCR ምርመራ ነው። የሳላይቫ (ምራቅ) ናሙና በትንሽ የምርመራ ቱብ ውስጥ ይሰበሰባል። የ 1-1.5 ሚሊሊቴር ምራቅ ናሙና ይሰበሰባል።

**ማን መመርመር አለበት?** መደበኛ የምልክት-አልባ ማጣሪያ ምርመራ ባሁን ጊዜ በትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ ላሉ ላል ተከተቡ ግለሰቦች በዲሲ ሄልዝ ይመከራል። በዚህ ጊዜ፣ ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ግለሰቦች መደበኛ የምልክት-አልባ ማጣሪያ ምርመራ ውስጥ እንድሳተፉ ዲሲ ሄልዝ አይመክርም። የ COVID-19 ፖዘቲቭ ኬዝ የቅርብ ተገናኞች እና የCOVID-19 ምልክቶች ያላቸው ሰዎች ምርመራ ባሁን ጊዜ ለሁሉም ግለሰቦች፣ የተከተቡ ወይም ያልተከተቡ ቢሆኑም፣ እንዲደረግ ዲሲ ሄልዝ ይመክራል።

**የምርመራ ፕሮግራሞቹ ምንድን ናቸው?**

- <u>መደበኛ የምልክት-አልባ ምርመራ፥</u> ተማሪው የCOVID-19 ቫይረስ ምርመራ ለመውሰድ በየሳምንቱ እንደ ዘፈቀደ የግለሰቦች ናሙና አካል ይመረጣል/ትመረጣለች።
- <u>የቅርብ ንክኪ/ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ምርመራ፥</u> ተማሪው በትምህርት ቤት መዋቅር ውስጥ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ያለበት ግለሰብ ጋር የቅርብ ግንኙነት እንደነበረው/ራት ከተለየ/ች፣ ከተጋለጠ/ች በኋላ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ለማግኘት ብቁ ይሆናል/ትሆናለች።
- <u>የምልክት-ያለው ምርመራ፥</u> ተማሪው/ዋ በትምህርት ቤት ውስጥ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምልክቶችን ካሳየ/ች የ COVID-19 ምርመራን ያጠናቅቃል/ታጠናቅቃለች።

በሌላኛው ገጽ ላይ ቀጥሏል



1050 First Street NE, Washington, DC 20002 • ስልክ፥ (202) 727-6436 TTY፥ 711 • osse.dc.gov

**የምርመራውን ውጤት እንዴት እና መቼ አውቃለሁ?**

የምራቅ ምርመራ ውጤቶች ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ወይም አዋቂ ተማሪ የሚገኘው በታማሚ ፖርታል አማካኝነት የሚገኝ ይሆናል። ውጤቶች በተለምዶ በ6-12 ሰዓታት ውስጥ ይደርሳሉ። እንዲሁም ምርመራው ፖዘቲቭ ከሆነ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ወይም አዋቂ ተማሪ ይጠራሉ። DC Health (ዲሲ ሄልዝ) እንደ COVID-19 ፖዘቲቭ ምርመራዎች መደበኛ አሰራሮች አካል ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ወይም አዋቂ ተማሪን ይከታተላል። የታማሚ ፖርታል የተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለብቻው ይቀርባል።

**የተማሪየን የምርመራ ውጤት ስቀበል ምን ማድረግ አለብኝ?**

<u>የተማሪው/ዋ የምርመራ ውጤት *ኔገቲቭ* ከሆነ</u>፣ ያ ማለት በዚህ ጊዜ ቫይረሱ የተማሪ ናሙና ውስጥ አልተገኘም ማለት ነው። ተማሪ ው/ዋ በዲሲ ሄልዝ የሚመከሩ ጭምብል መልበስ፣ የእጅ ንጽህና መጠበቅ እና ማህበራዊ ርቀት ልምምዶችን መቀጠል አለበት/ባት። ተማ ሪው/ዋ ኔገቲቭ የምርመራ ውጤት ከደረሰው/ሳት ግን ምልክት ካለብተ/ባት ወይም ለ COVID-19 ተመርምሮ ፖዘቲቭ የሆነ ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ካለው/ላት፣ ልጅዎ መቼ ወደ ትምህርት ቤት እንደሚመለስ/እንደምትመለስ በተመለከተ ከዲሲ ሄልዝ እና ትምህርት ቤትዎ የተሰጡ ሁሉም መመሪያዎችን መከተል አለባችሁ። ተማሪው/ዋ የ COVID-19 ምልክቶችን ካሳየ/ች፣ የተማሪው/ዋን የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር መደወል አለብዎት፣ የምርመራ ውጤቶች ምንም ቢሆኑም።

<u>የተማሪው/ዋ የምርመራ ውጤቶች *ፖዘቲቭ* ከሆኑ</u>፣ ያ ማለት ተማሪው/ዋ ላይ ቫይረሱ አለ እና ሊያሰራጭ/ልታሰራጭ ይችላል/ ትችላለች። እባክዎ በአስቸኳይ የተማሪው/ዋን የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያነጋግሩ። ተማሪው/ዋ ቤት መቆየት እና ከዲሲ ሄልዝና ትምህርት ቤትዎ የተሰጡ የጤና እና የትምህርት ቤት መመሪያዎችን መከተል አለበት/ባት። የምርመራ ውጤቱ ሲደርስ፣ ተማሪው/ዋ ካምፓስ-ውስጥ ካለ/ች፣ ከትምህርት ቤት እስከሚወሰዱ ድረስ፣ ወደ ለብቻ ማውጣት በታ ይወሰዳሉ።

እንደ ማንኛውም የላቦራቶሪ ምርመራ፣ ያለ-መደምደም፣ የውሸት ፖዘቲቭ ወይም የውሸት ኔገቲቭ ውጤቶች ትንሽ ስጋት አለ። ጤናዎን በተመለከት ማንኛውም ሀሳብ ከገባዎት፣ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ምልክቶች መኖርን ጨምሮ፣ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ዎን እንዲያነጋግሩ በጥብቅ ይበረታታሉ።

**ተጠያቂነት**

ዲስትሪክቱ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ሠራተኞቹ፣ እና ኤጀንቶቹ ከዲስትሪክቱ የከተማ-ደረጃ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ እርምጃዎች ወይም መተላለፎች የሲቪል ተጠያቂነት ነጻ ይሆናሉ፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ ሆን ተብሎ የሚሰራ በደል፣ ከባድ ቸልተኝነት፣ ወይም በፍላጎት የሚፈጸም የስነ-ምግባር ጉድለት በስተቀር።

**መረጃ/ደታ እና ሪፖርት ማድረግ**

ከዚህ ቅጽ እና ከምርመራዎች ውጤት የሚገኝ ደታ እንደ COVID-19 ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች አካል ይሰበሰባል እና ለተገቢ ትምህርት ቤት እና የጤና ባለስልጣናት ሊጋራ ይችላል። ተማሪው/ዋ ለ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ተመርምሮ/ራ ፖዘቲቭ ከሆነ/ች የተማሪው/ዋ ማንነት ለሌሎች አይገለጽም።

**ከተሳትፎ ለመውጣት እንዴት መምረጥ እችላለሁ?** ከምረመራ ፕሮግራሙ ለመውጣት መምረጥ ከፈለጉ፣ ለተማሪዎ (ወይም እርስዎ፣ የ18 ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ተማሪ ከሆኑ) በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን የመውጫ-ምርጫ ቅጽን መሙላት እና መመለስ አለብዎት። የመውጫ-ምርጫዎ ይመዘገባል እና ተማሪዎ ለምርመራ አይመረጡም ወይም ብቁ አይሆኑም። ይህ የመውጫ-ምርጫ ቅጽ ለ 2021-22 ትምህርት ዓመት ተቀባይነት አለው፣ተማሪዎ (ወይም እርስዎ፣ እድሜዎ 18 እና ከዚያ በላይ የሆነ ተማሪ ከሆኑ) የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ እንድቀበል/እንድትቀበል እንደሚፈልጉ የሚገልጽ የጽሁፍ ደብዳቤን ወይም ኢሜይል ለተማሪዎ ትምህርት ቤት በመላክ በማንኛ ውም ጊዜ ስምምነትዎን ማንሳት ይችላሉ።

## ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ የመውጫ-ምርጫ ቅጽ

**የመገኛ መረጃ** | በወላጅ/አሳዳጊ የሚሞላ (ወይም በተማሪ፣ 18 ወይም ከዚያ በላይ እድሜ ከሆነ/ች)

| የተማሪ የአያት ስም፥ | የተማሪ የመጠሪያ ስም፥ | የትውልድ ቀን፥ |
|---|---|---|

| የትምህርት ቤት ስም፥ | ቀጠና/ዋርድ፥ |
|---|---|

| የቤት አድራሻ፥ | አፓርታማ፥ | ከተማ፥ | ክልል/ስቴት፥ | ዚፕ፥ |
|---|---|---|---|---|

| የወላጅ/አሳዳጊ ስም፥ | ስልክ፥ | ኢሜይል፥ |
|---|---|---|

| የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ ስም፥ | የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ ስልክ፥ |
|---|---|

ከታች በመፈረም ፣ እኔ ይህን እያልኩ ነው፥

- ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም የማንበቢያ ወረቀት አጠቃላይ እይታ ውስጥ የቀረበውን መረጃ አንብቤ ተረድቻለሁ እና ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ ፍላጎት የለኝም።

- ትምህርት ቤት-መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮሮናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ውስጥ ባለመሳተፍ፣ ተዛማጅ ትምህርት ቤት እና የጤና ባለስልጣናት በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ መኖር እና ስርጭት በተመለከተ ያነሰ መረጃ እንደሚያገኙ እረዳለሁ።

- ተማሪው/ዋ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ ኬዝ የቅርብ ንክኪ ያለው/ላት ተደርጎ/ጋ ከተለየ/ች ወይም ምልክት -አልባ ከሆነ/ች፣ የመውጫ-ምርጫ ካልተነሳ በስተቀር ተማሪው/ዋ ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ የምርመራ ፕሮግራም ሥር ለመመርመር ብቁ እንደማይሆን/እንደማትሆን እረዳለሁ።

- ይህን ቅጽ በነጻ እና በገዛ ፈቃዴ ነው የፈረምኩት፣ እና ከታች ለተጠቀሰ ተማሪ (ወይም ለእራሴ፣ እድሜየ ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ተማሪ ከሆንኩኝ) ውሳኔዎችን ለማሳለፍ ህጋዊ ስልጣን አለኝ።

- በማንኛውም ጊዜ ውሳኔየን ለውጬ ትምህርት ቤት መሰረት ያደረገ የ COVID-19/ኮርናቫይረስ ምርመራ ፕሮግራም ውስጥ ለመሳተፍ ልመርጥ እችላለሁ። ይሁን እንጂ፣ የእኔ የመውጫ-ምርጫ ለ 2021-22 የትምህርት ዓመት ተቀባይነት አለው፣ ይህን የመውጫ-ምርጫ እንዳነሳሁ ከተማሪየ ትምህርት ቤት ለተወከለ ጠሪ ሰው በጽሁፍ ካሳወቅኩት በስተቀር።

የወላጅ/አሳዳጊ የስምምነት ፊርማ (ተማሪ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ/ች) ቀን (ወወ/ቀቀ/ዓዓዓዓ)

(እድሜው/ዋ ከ18ዓመታትወይም ከዚያበላይ ከሆነ)የተማሪ ፊርማ ቀን (ወወ/ቀቀ/ዓዓዓዓ)



1050 First Street NE, Washington, DC 20002 • ስልክ፥ (202) 727-6436 TTY፥ 711 • osse.dc.gov